

# የኩዊር ደስታ





መጋቢት 2016
ቅፅ ፬ | ቁጥር ፩

ንስንስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ
በየሩብ ዓመቱ በኩዊር ኢትዮጵያ
የምትታተም መጽሔት
Nisnis - A quarterly magazine
published by Queer Ethiopia
focusing on LBQ issues

# QUEER ETHIOPIA
# ኩዊር ኢትዮጵያ

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ' ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሳይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።


queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

t.me/queeret



# ማውጫ




03



04 - 11



12 - 17



18 - 21



22 - 25



26 - 29



30 - 33



34 - 37



38 - 41

የኩዊር ደስታ ለእናንተ ምን ማለት ነው?
42

# የአርታዒያን መልዕክት

እንኳን የኩዊር ደስታን ወደምናከብርበት ፲ኛው የንስንስ እትም መጡ! በዚህ እትም በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ውስጥ ስላለው ደስታ እና ሀሴት እናስሳለን።

የኩዊር ደስታ ከስሜት በላይ ነው። የኩዊር ደስታ ድርጊት ነው። ፅናትን የሚፈጥር ነው። ለማህበረሰባችን ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታን፥ የሚረዳ ማህበረሰብ እንድንፈጥር ያስችለናል። እንዲሁም ለራሳችን እና ለማህበራዊ ተቀባይነት ፅናት ኖሮን የሚያቆየን ነው።

የኩዊር ደስታ አለማቀፋዊ ፅንሰሀሳብ ሲሆን ከፆታዊ ማንነት እና የፆታ መገለፃዎች በላይ የሆነ ነገር ነው። በመሰናክሎች በተሞላው የኩዊር ህይወታችን ውስጥ ባሉት አዎንታዊ ነገሮች ላይ እንድናተኩር ያስችለናል። በጥላቻ በተሞላና ራሳችንን መቀበል ራሱ ከባድና ውጣ ውረድ የሞላበት እንዲሆን በተደረገበት ሀገር ብንኖርም መልካሙን የሚያመላክተን የኩዊር ደስታችን ነው።

ቃለመጠይቅ ያደርግንላት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዋ ቬሮኒካ ራሷን 'ስለመቀየር' የአእምሮ ሀኪም ጋር ስለመሄዶ ትነግረናለች። ደስታዋ በመጨረሻ ራሷን መቀበል እና ምንም ችግር እንደሌለባት ማመኗ ነው። ሌክሲ ለረዥም ጊዜ የኩዊር መብቶች ታጋይ ሆና የሰራች ሲሆን ሰዎች በእኛ ፅሁፎች እንደታዩ ተቀባይነት እንዳገኙ እና ድጋፍ እንዳላቸው እንዲሰማቸው እንዳደረኩ ሳውቅ ደስታን ይሰጠኛል ትላለች።

የኩዊር ደስታንና ነፃነት ፍለጋችን ውስጥ ጥበብም ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። በፀሎት የኩዊር አርቲስት ስትሆን በስራዎቿ የኩዊር ማህበረሰቡን ለማስተዋወቅ መስራቷ ደስታን እንደሚፈጥርላት ትናገራለች። 'ኩዊር ጥበብ ተርበን ወይም ተጠምተን ምግብ ወይም ውሃ እንደማግኘት ነው ትላለች'። አንድ አምደኛችን እንደምትለው የኩዊር ጥበብ ራሳችንን ለመግለፅ' ለመረዳት እና በቀላሉ ለማስደሰት የምንመለከትበት መስታወት ነው።

የኩዊር ደስታ ከፖለቲካ ወይም ጥበብ በላይ ነው፤ ፍቅራችንም ለደስታችን ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። አንድ አምደኛችን በሁለት ሴቶች መሀል ያለውን ፍቅር ትገልፅልናለች። ይህን ታሪክ በምናነብ ሰአት በመሃላቸው ያለውን ፍቅርና መተሳሰብ ሳይሰማን ማለፍ ከባድ ነው።

ሌላዋ አምደኛችን በኢትዮጵያ ያለውን ጥላቻ ሸሽታ በናይሮቢ ቆይታዋ ነፃነትን እና የፍቅርን ደስታ እንዴት እንዳጣጠመችው ትነግረናለች። ፍቅራቸው በእንግዳ ሰዎች ሲከበር በማየቷ የተሰማትን ደስታ ታጋራናለች። 'አብረን ስንራመድ ሰዎች የምናምር ጥንዶች እንደሆንን ይነግሩናል ትላለች።

የኩዊር ደስታ ድርጊት ነው - ራሳችን እና ማህበረሰባችንን በዘላቂነት የምናከብርበት መንገድ ነው። በየቀኑ ብዙ ከባድ መሰናክሎች ቢያጋጥሙንም በሀዘን ከመዋጥ ይልቅ ህይወትን በደስታ ለመኖር ያለንን ቁርጠኝነት የምናሳይበት ነው።

ይህ የንስንስ እትም የኩዊር ደስታ ላይ በማተኮር 'ኩዊር ነን፤ ደስተኞች ነን' የሚለውን መሪ ቃል በደስታ ያጋራል! ይህ እትማችን የየራሳችሁን የደስታ ምንጮች በማሰብ ጥሩ ስሜትን እንደሚፈጥርባችሁ ተስፋ እናደርጋለን።

እንደተለመደው በዚህ መጽሔት ዝግጅት ላይ የተሳተፉትን ሁሉ እናመሰግናለን፡፡ ታሪካቸውን እና የጥበብ ስራዎቻቸውን ላካፈሉን እና ለሚያነቡልን ሁሉ ምስጋናችን ከልብ ነው፡፡

በዚህ እትም እንደምትዝናኑ እና ደስታን ይዞላችሁ እንደሚመጣ ተስፋችን ነው!



# የኲዊር ደስታ፥ ውብ እና ጠንካራ ማህበረሰባችን

*የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች እና ትራንስ ጥላቻ በጨመረበት በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ኲዊር ማህበረሰብ ደስታን ለማግኘት የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማል። ይህ ታሪክ ተስፋን ለመስጠት በማለም የተዘጋጀ ነው። የኲዊርነት ደስታ በጥላቻ በተሞላቸው ሀገራችን ውስጥም ቢሆን ገኖ መታየት እንደሚችል ያመለክታል። ከሶስት ጠንካራ ሰዎች ጋር ባደረግናቸው ቃለመጠይቆች ስለልምዳቸው፤ ደስታን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል እንዲሁም ታፍኖ መኖርን ያልመረጠ እና በጀግንነት በተለያዩ መንገዶች ራሱን ስለሚገልፀው ማህበረሰባችን ብዙ ብለውናል።*





**ቬሮኒካ፡ የራስን ፍለጋ እና ራስን መቀበል ጉዞ**

የመጀመሪያውን ቃለ መጠይቅ ያደረግነው ከክልሎች ዋና ከተማ ከአንዱ ከመጣችው እና የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ከሆነችው ቬሮኒካ ጋር ነው። ቬሮኒካ ራሷን የማወቅ እና የመቀበል እውነተኛ የፅናት ጉዞ ጀምራለች። በፆታዊ ማንነቷ እና በፆታ አቀራረቧ ምክንያት የሚደርስባትን የማህበረሰብ ጫናዎችን እና ጥላቻን እንዴት እንደተጋፈጠችው ልምዷን አካፍላናለች። መጀመሪያ ላይ ማንነቷን ለመቀበል ስለከበዳት እና 'ኖርማል' መሆን በመፈለጓ የአእምሮ ህክምና ባለሙያን እስከማማከር ደርሳ ነበር። እናም በእውነቱ "ለመለወጥ" እና "የተለመደ" እንድትሆን ለመርዳት ወደ የሥነ-አእምሮ ሐኪም የመቅረብ አደጋ ነበራት። የኢትዮጵያ ኩዊር ማህበረሰብ የሚያጋጥመውን ብዙ ፈተናዎች እና ትግሎችን ጉዞዋ ማሳያ ነው።


የአእምሮ ህክምና ባለሙያዋ ሌዝቢያን የሆንሽበት ምክንያት የሆርሞን ችግር ነው በማለት መስተካከል እንዳለባት ነገራት። ማንነቷን ለመቀየር እና ሃኪሙ እንዳለው 'ኖርማል' ለመሆን ከሞከረች በኋላ ቀስ በቀስ ወደራሷ መመለስ ጀመረች።

'መጥፎ ነገር እንደሆነ እንሰማ ነበር። የተለያዩ ቪዲዮዎች እና ድራማዎችን በማሳየት ሌዝቢያን መሆን መጥፎ እንደሆነ እንዳምን ተደርጌ ነበር' ስትል ቬሮኒካ ትናገራለች። ስለኩዊር ማንነቷ ግራ ከመጋባቷ የተነሳ ብዙ ታለቅስ እንደነበር ታስታውሳለች። የለውጥ ጉዞዋ የተጀመረው ብትፀልይ እና ሃኪሙ የመከራትን ብታደርግም ለሴቶች ያላትን ስሜት መቀየር እንደማትችል ከተረዳች በኋላ ነው።

የፈጣሪ ቸርነት እርግጠኝነት እና በራስ መተማመንን እንደሰጣት ትገልፃለች። ራሷን ለመቀበል ያን ያህል ባትሰቃይ ትመርጥ እንደነበር ብትገልፅም ዛሬ ያለችበት ለመድረስ አስፈላጊ እንደነበር ግን ታምናለች።

"ምንም እንኳን በጣም የሚያም የነበረ ቢሆንም ያንን መንገድ ማለፌ ዛሬ ላይ ስለራሴ ምንም ጥያቄ እና ጥርጣሬ እንዳይኖረኝ ረድቶኛል" ትላለች።

የቬሮኒካ ጉዞ ራስን ወደመቀበል ያለው መንገድ ከባድ እንደሆነ የሚያስታውሰን ነው። በተጨማሪም በጥላቻ የተሞላ ሀገር እንደመኖራችን የሚሰማን በራስ ያለመተማመን ስሜት ራሳችንን ወደመቀበል እና ደስተኝነት የምናደርገው ጉዞ አንዱ አካል መሆኑን ያሳያል። ቬሮኒካ ዛሬ ያገኘችው የኩዊርነት



ደስታ የመጣው ራሷን መሆን ከመቻሏ እና ጥርጣሬዋ በመጥፋቱ እንደሆነ ትናገራለች። ከቃለመጠይቃችን በኋላ ከፍቅረኛዋ ጋር በደስታ እና በኩራት አብረው ሲራመዱ የወንዳወንድ መገለጫ ያላት ሌዝቢያን አለምን ለመጋፈጥ የሚያደርጉትን ጉዞ አይተንበታል።

**ሌክሲ፡ ማህበረሰብ እና ግንኙነት**

በሁለተኛ ቃለመጠይቃችን የኢትዮጵያ ኩዊር ማህበረሰብ አባል ከሆነችው እና ለኩዊሮች ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታን ለመፍጠር ከምትጥረው ሌክሲ ጋር አውርተናል። ከ10 አመታት በላይ በታጋይነት የቆየችው ሌክሲ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት፤ በመፃፍ፤ የድጋፍ ቡድኖችን በማደራጀት እና አብሮነትን የሚያጠናክሩ ስራዎችን ትሰራለች።

ሌክሲ የማህበረሰብ ድጋፍ በተለይም በጥላቻ በተሞላ አካባቢ ውስጥ የኩዊር ደስታን ለመፍጠር ስላለው ጠቀሜታ አስረግጣ ትናገራለች። በተለይም ከኩዊር ቤተሰብ ጋር እንደምትሰራ የሙብት ታጋይ እንዲህ በማለት ትናገራለች። 'ትልቅ ደስታ የሚሰጠኝ ታሪካችንን መናገር ነው። ችግራችንን እና ስኬታችንን የሚገልፁ ታሪኮችን በመንገር ድምፃችንን ማሰማት እና መኖራችንን እና የእኛን እውነት ማሳወቅ እንችላለን።'

በእርግጥ የኩዊር ንቅንቄን እንደኢትዮጵያ ባለ ሀገር ማዘጋጀት ብዙ ችግሮች እና አደጋዎች አሉት። ሌክሲ እንደምትለው አዎንታዊ ተፅእኖን መፍጠር እና ማህበረሰብን ማደራጀት በከባድ ጊዜያት ውስጥም ፍቅር፤ ተቀባይነት እና ፅናት እንደሚያሸንፉ የሚያሳይ ነው።

ኩዊር ሰዎች መገለል፥ ተቀባይነት ማጣት እና ጥቃት በሚያስተናግዱበት ማህበረሰብ ውስጥ ደህንነታቸው ተጠብቆ ራሳቸውን መሆን የሚችሉበትን ቦታ መፍጠር አስደሳች ነው። እነዚህ ቦታዎች የቤተሰባዊነት ስሜትን ለመፍጠር እና እርስበርስ መደጋገፍን ለማበረታታት አስፈላጊ ነው።

"አንድ ሰው ፅሁፎቻችንን ተመልክቶ ብቻውን እንዳልሆነ፤ ልክ እንደሆነ እና እንደምንደግፈው እንዲሰማው ማድረግ መቻላችንን ማሰብ

ደስታን ይሰጠኛል። በጉዟችን ብቻችንን እንዳልሆንን እና ያሳለፍነው ጊዜ ዋጋ እንዳለው ያስታውሰናል" ስትል ሌክሲ የኲዊር ደስታዋ ከትግሏ ጋር እንደሚገናኝ ትገልፃለች።

> … ዛሬ ላይ ስለራሴ ምንም ጥያቄ እና ጥርጣሬ እንዳይኖረኝ ረድቶኛል።
>
> – ቬሮኒካ

**በፀሎት፡ ነፃነትን በጥበብ መግለፅ**

ሶስተኛ እና የመጨረሻ ቃለመጠይቃችን ከበፀሎት ጋር ነው፤ በፀሎት ኲዊር አርቲስት ስትሆን ችሎታዋን የራስ ፍቅርን እና ትግልን ለመግለፅ ትጠቀምበታለች። ጥበብን በመጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ወግ አጥባቂ የማህበረሰብ ህጎችን በመጋፈጥ ኲዊር ማንነቷን ለማክበር እና ማህበረሰቡን ለመወከል ትጠቀምበታለች። በፀሎት ስራዎቿን በፌስቡክ የምታጋራ ሲሆን ለኢትዮጵያዊ ኪውሮች ተስፋ፤ ደስታ እና ተቀባይነትን ለመስጠት ትጠቀምበታለች። በስእሎቿ ለኢትዮጵያዊ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ ታልማለች።

'የኲዊር ጥበብ የምንፈልገውን ለማለት የምንጠቀምበት መሳሪያ ነው። በሀገራችን እንደኲዊር ማህበረሰብ የምንፈልገውን በአደባባይ ማለት አንችልም ምክንያቱም አደጋ ይጥለናል። ጥበብ ግን ለብዙሀኑ ህዝብ እንዳለን እና ሊቀበሉን እንደሚገባ ለመንገር ይጠቅመናል።'

የኲዊር ሰዎች ጥበብ እና ስለኲዊር ሰዎች የሚሰሩ የጥበብ ሰዎች ማህበረሰቡን ለማጠናከር እጅግ አስፈላጊ ነው። ለኲዊር መብቶች የምትታገለው በፀሎት ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ንግግርን ለመፍጠር አንዱ መንገድ እንደሆነ ትገልፃለች። በስራዎቿ ስለፍቅር፤ የፍቅር ህይወት፤ ስራ እና ጥንካሬ ውይይቶች እንዲደረጉ ትጋብዛለች። የበፀሎት ስራዎች የኲዊር ማህበረሰብ ተወክሎ በማይታይበት ሀገር ውስጥ መኖራቸውን ለማሳየትም ያገለግላሉ።

'የኲዊር ጥበብ ለሁሉም ሰው የምታሳይው ነገር አይደለም በነፃነት ልትሸጪው አትችይም ወይም ይፋ አታወጪውም፥ ነፃነትን ይጠይቃል። የኲዊር ጥበብ ርቦሽ ወይም ጠምጦሽ ምግብና ውሀ እንደመፈለግ ነው። ስስል የሚሰጠኝ ስሜት ያንን ነው። ለምሳሌ አንድ ሴት ፍቅር ውስጥ ሆና ብስል እያሰብኩ ያለሁት ያንን ስለሆነ ነው' በማለት በፀሎት ትናገራለች።

ስራዎቿ ደስታን እና ጥንካሬን በእውነተኛ ማንነቷ ውስጥ እንድታገኝ አድርገዋታል። 'ለኔ የኲዊር ጥበብ ከደስታም በላይ ቋንቋዬም ነው። ራሴን የምገልፅበት እና ማን እንደሆንኩ ለማያውቀው አለም ራሴን የማሳውቅበት ነው።'

**የኲዊር ደስታን ማክበር**

የኲዊር ደስታ የፅናት እና የአይበገሬነት መንፈስ የሚታይበት ነው። ብዙ ችግሮች ቢኖሩም የኲዊር ማህበረሰቡ ጥንካሬን ምቾት እና ደስታን ፍለጋ አላቆመም።

በቬሮኒካ ሌክሲና በፀሎት ታሪኮች ውስጥ የፅናት፤ እውነተኛነት

እና ማህበረሰቡን ጥንካሬ አይተናል። በወግ አጥባቂ ማህበረሰብ ውስጥ ደምቆ የሚታይ የኩዊር ደስታን ለመፍጠር ደህንነታቸው የተጠበቁ ቦታዎችን ያመቻቹ ጠንካራ ኢትዮጵያዊ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ምሳሌ ናቸው።

በኢትዮጵያ ኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኘው ደስታ ግላዊ ስኬት ብቻ ሳይሆን አካታች፣ ተቀባይ እና ተሻጋሪ ለሆነ ህዝብ የተስፋ ጨረር የሚሆን ነው። ደስታችን ፍቅር ምንም እንደማይገድበው እና እያንዳንዱ ሰው ፆታውን በፈለገው መንገድ መግለፅ እንደሚችል እንዲሁም በየቀኑ የሚያጋጥመን መገለል እና ፍርሀት ቢኖርም እውነተኛ ማንነታችንን ማክበር እንደምንችል የሚያስታውሰን ነው።

ሌክሲ እንዳለችው 'ድምፃችንን በምናሰማበት፣ መኖራችንን በምናሳውቅበት እና ታሪካችንን ራሳችን በምንናገርበት' በዚህ ጉዞ የቃለመጠይቃችን እንግዶች ታሪክ ራሳችንን እንድቀበል ማንነታችንን እንድናከብር እና ተቀባይነትን የምናገኝበትን መንገድ እንደሚያግዘው ተስፋ እናደርጋለን።

የማህበረሰባችን ፅናት ደምቆ የሚታይ ነው። የቬሮኒካ ራስን ፍለጋ እና በኋላም የባለሙያ መጥፎ ምክር እንኳን ኖሮ ራሷን መቀበል መቻሏ ራስን መቀበል አስፈላጊ መሆኑን ያሳየናል።  የሌክሲ ለማህበረሰቡ መገናኛ መንገዶች ለማግኘት መስራቷ ለኩዊር ደስታ የመደጋገፍን አስፈላጊነት የሚያመላክት ነው። የበፀሎት የጥበብ ትግል የኩዊር ማንነትን በማክበር፣ ሌሎችና ራሷን የሚወክላቸውን ስራ፣ ጥንካሬ እና ደስታን እንድታገኝ አስችሏታል።

እነዚህ የፅናት፣ ማህበረሰብ፣ ፍቅር እና የማክበር ታሪኮች የኢትዮጵያን የኩዊር ማህበረሰብ ጥንካሬ የሚያሳይ ነው። የምንጋፈጠው ጥላቻና ችግር ማንም ሊነጥቀን የማይችለውን ደስታችንን እንደማይወስድብን ያስታውሰናል።

> "ትልቅ ደስታ የሚሰጠኝ ታሪካችንን መናገር ነው።
>
> -ሌክሲ"



"የኩዊር ጥበብ ርቦሽ
ወይም ጠምጦሽ
ምግብና ውሀ
እንደመፈለግ ነው።

– በፀሎት"



የኲዊር ደስታ
የፅናት እና
የአይበገሬነት
መንፈስ
የሚታይበት ነው።




## - አሌክስ -

የኩዊር ማንነቴን የምወደው ስለሴቶች በደንብ እንዳውቅ እና እንዳከብራቸው ስላደረገኝ ነው። ስስነታቸው፤ ለስላሳ ከንፈራቸው እና ሽታው ቀልቤን ይገዛዋል። ደግነታቸውን እና መስጠት መውደዳቸው ለኔ ቦታ አለሁ። የምንፈጥረው የስሜት መረዳዳት ደስታን ይሰጠኛል። በምናጋራው ስለአለም ያለን አመለካከት እና ዋጋችንን ባልተረዳ አለም ላይ ለኛ የሚሆን ቦታን ስለማግኘት ባለን ፍላጎት ውስጥ እጠፋለሁ። የሴት ልጅ ውበት ያስገርመኛል። ሴቶችን ማፍቀር በመቻሌ እና በእነሱም መፈቀር በመቻሌ አመስጋኝ ነኝ።




## - በፀሎት -

እኛ አሁን ባለንበት የደስታችን ምንጭ የምለው እኛን የመሰለ ሰው ማየት ነው። ፍቅረኛ ወይንም ዝም ብሎ ጓደኛም ሊሆን ይችላል። ብቻችንን አለመሆናችን ስናቅ እና እራሳችንን መቀበል ስንጀምር ይሄ የደስታችን ምንጭ ነው። አብዛኛውን አርቴን የምሰራው ከዚህ ስሜቴ ተነስቼ ነው። ሴቶች ወይንም ወንዶች ለእርስ በርስ ያላችውን affectionናቸውን ሲገልፁ ማየት ደስ ይለኛል። ለእኔ የደስታዬ ምንጭ ኩዊር አርት መስራት ነው።




## - ኤስ -

ራሴን መሆን መቻሌን እወደዋለሁ የህብረተሰቡን ባህላዊ ህጎች መከተል አያስፈልገኝም። እንደኛ ባለ ወግ አጥባቂ ማህበረሰብ ውስጥ ስንኖር ልንከተላቸው የሚገቡ ህጎች እና እንድናደርግ የሚፈልጓቸው ነገሮች አሉ፣ ለምሳሌ ማግባት እና ልጅ መውለድ ወይም ሴትን እንደ ሴት መልበስ። ተቀባይነት እንድናገኝ ወደሚያውቁት ነገር ይገፋፉናል። ኩዊር መሆኔን የምወደው እኔ መሆን በመቻሌ ነው። የፈለኩትን ልብስ ለብሼ የፈለኩትን ሰው እወዳለሁ የኔ የምላቸው ሰዎች ይቀበሉኛል። ምንም እንኳን አብዛኛው ሰው በፊት እግር ኳስ ተጫዋች የነበርኩ ወይም የወንድ አለባበስ ያለኝ ስፖርተኛ ስለሆንኩ እንደሆነ ቢያስብም ከቅርብ ጓደኞቼ እና ቤተሰቦቼ ጋር፣ ደስተኛ የምሆነው ሀሳቤን እና ማንነቴን ከነሱ መደበቅ ስለሌብኝ ነው። ለነሱ እኔ ከነሱ የሚለየኝ ነገር የለም። በትክክል የሚሰማኝን ለመናገር እና ለመሆን ምንም አያስፈራኝም።




## - ዮሃና -

የኔ ኩዊር ደስታ ሴቶች ናቸው፤ ውብ ፍጡሮች ናቸው አማላይ እና ቆንጆ ናቸው እና በአንድ ደካማ እና ሀይለኛ የሚያደርገኝ አቅም አላቸው። ያላቸው ውበት ያስደስተኛል ያንን ማየት በመቻሌ ደግሞ በፍቅራቸው እወድቃለሁ። ኩዊር ስለሆንኩ ብቻ ሳይሆን ሴቶች ከፍ ያለ ደረጃ ደርሰው ሳያቸው ደስ ይለኛል። ሰዎች ሴቶች እርስ በርስ ጥሩ አይደሉም፥ ስልጣን ላይ ሴት ማየት አይፈልጉም ወይም ሴት አስተማሪ አትወደድም ይላሉ እኔ የሚሰማኝ ግን የዛ ተቃራኒ ነው። ሴቶችን በስልጣን ላይ ሳይ ደስ ይለኛል።




## - ፅዮን -

የኔ ኩዊር ደስታ ፅናቴ ነው። ስህተት በሚለኝ ማህበረሰብ ውስጥነው የምኖረው። ብሰማቸው ኖሮ ከብዙ ጊዜ በፊት ማንነቴን ቀይሬ ሴት ያደረገኝን የእኔነቴን ክፍል ለመደበቅ እሞክር ነበር። በኩራት እና ያለፍርሀት ራሴን መሆን መቻሌን እወደዋለሁ። የኩዊር ደስታዬ አይኔን ሳልሰብር ከሞት ጋር መፋጠጤ እና ከነማንነቴ መኖር መቻሌ ነው። እኔን የሆንኩት በፍርሀት ተከበንም እኛነታችንን የምንቀበል የኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ በመሆኔ ነው። ሌሎች ሴቶች እና ለመረጥኳቸው ቤተሰቦቼ ያለኝ ፍቅር ያኖረኛል። የኩዊር ደስታዬ ቤተሰቤ ነው። ምክንያቱም ምንም ቢፈጠር እኔነቴ የማይቀየረው አለን የሚለኝ የኩዊር ማህበረሰብ ስላለኝ ነው። ማህብረሰቤ ፅናቴ የሚቻል እንደሆነ እንዲሰማኝ ያደርጉኛል።



# የኢትዮጵያዊ ኩዊር ደስታ

**- ሃበን -**

የኔ ኩዊር ደስታ የፆታ ሚናዎችንና ሌሎች የሚጠብቁብንን ነገሮች ችላ ለማለት እና ሕይወቴን በተቻለ መጠን በትክክል ለመኖር ስመርጥ ነው። የምፈልገውን ለመልበስ ስመርጥ፣ ሰዎች ወንድ ናት ብለው ሲገምቱ "ሴት ነኝ" ብዬ ስናገር፣ እና ሰዎች ሊሳለቁብኝ ሲመርጡ እንኳ ካንገቴ ቀና ብዬ ስሄድ ደስተኛ ነኝ ። ሌሎች ስለ እኔ ምንም ቢናገሩ እና ምንም ያህል እኔን "ኖርማል" ሊያደርጉኝ ቢሞክሩም እኔ ማንነቴን ማክበር እመርጣለሁ. እስቃለሁ፣ እኔን ከሚመስሉኝ ሰዎች ጋር ጊዜ አሳልፋለሁ እና ከእውነተኛ ማንነቴ ያነሰ ለመሆን ፈቃደኛ አልሆንም። ያኔ ነው ለውስጤ የደስታ ስሜት የሚሰማኝ።

# ደስታን ማነገብ፡



# የኩዊር ነፃነት ምሽት



ወንዶቹ እየደነሱ፤ እያወሩ እና ተቃቅፈው እየተሳሳሙ ነው። በዛ ሁሉ ላብ እና ግርግር ውስጥ ሀሳቧ በጭንቀት የተሞላው እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም። መሬቱ ተከፍቶ ይውጣቸው ይሆን? ጠባቂዎቹና የሚጨፍሩት ሰዎች ይሰድቧቸው ወይ ይመቷቸው ይሆን? ቢያንስ ካልያዝናቸው ብሎ የሚታገል አይጠፋም ብዬ ጠብቄ ነበር።

አንድ ጓደኛዬ እኔና ፍቅረኛዬን አልኬሚስት ወደሚባል ባር ወስዳን ነው። በመሀል ናይሮቢ በተለይ የፈጠራ ስራዎች ማሳያነት ይታወቃል። በከተማው አለ የሚባለው ይህ ቤት በምግብ፥ ፋሽን፥ ሙዚቃ እና ሌሎችም ስራዎች ላይ የተሰማሩ ብዙ የንግድ ሰዎች መገኛም ነው። ድህረገፃቸው ጥበብን ለሚወዱ ቤት ነው፥ ስኬት የሚገኘው ከባድ ውሳኔዎችን በመወሰን ነው ብሎ ይገልፃል፤ ለኔ ግን ለየት ብሎ የታየኝ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ወንዶች በነፃነት ራሳቸውን የሚገልፁበት ቤት መሆኑ ነው። የታችኛው የቤቱ ክፍል ለተቃራኒ ፆታ አፍቃሪዎች እና የላይኛው ደግሞ ለተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ወንዶች የተመቻቸ ይመስል በነፃነት ሲደንሱ እና ሲጠጡ ያመሻሉ።

ፍቅረኛዬ እና ጓደኛችን ሲደንሱ ከዳር ቆሜ እየተመለከትኩ ነው። ልቤ አብሯቸው ቢደንስም ዳንስ የማይችሉት እግሮች የዳንስ ወለል መሰል ወደ ሆነው ቦታ አለፍ ብዬ እንድሄድ አልፈቀዱልኝም። ሁሌም ተስፈኛ የሆነችው ፍቅረኛዬ ዳንስ ልታስተምረኝ ወይ ቢያንስ እንቅስቃሴዬ ሰው እንዳያስደነግጥ ለማድረግ እየሞከረች ነበር። በህዝብ መሀል አብረው እንደሚደንሱ ሁለት ሴቶች ሳንሳቀቅ ግንኙነታችን ለሚያየን ግልፅ ሆኖ መዝናናታችንን ቀጠልን።

እይታዬን ከህዝቡ ለመንቀል የተወሰነ ጊዜ ፈጅቶብኝ ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚኖር ሰው ኩዊር ሰዎች በአደባባይ ሲደንሱ እና ሲጫወቱ ማየትን መልመድ ቀላል አልነበረም። እነዚህ ወንዶች በነፃነት እንደማንኛውም ሰዎች በምሽት ለመዝናናት የሚችሉበት ደህንነታቸው የተጠበቀበት መኖሩን በማወቅ ተገረምኩ። ትክክለኛው ነገር ያ መሆኑን አጥቼው አልነበረም፥ ግን በጥላቻ በተሞላ ማህበረሰብ ውስጥ ለረዥም ጊዜ መኖር ትክክለኛው ነገር ምን እንደሆነ እንዲጠፋ የማድረግ አቅም አለው። ወንዶቹ እንደማንኛውም አዲስ አበባ እንደሚገኝ የተቃራኒ ፆታ አፍቃሪዎች ባር ውስጥ እንዳለ እና ሌላ የሚያሳስባቸው ነገር እንደሌለ ሆነው ሲዝናኑ ማየት ደስ የሚል ነበር።

ጓደኛችን ትራንስ ሴት ስትሆን ቤቱ ውስጥ የነበሩትን አብዛኞቹን የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ወንዶች ታቃቸው ነበር፥ ከተወሰኑት ጋርም አስተዋወቀችን። ቆየት ብለን የከነከነንን ጥያቄ ጠየቅን። እንደኩዊር ሴቶች ሌሎች እንደኛ ያሉ ሴቶችን ለመተዋወቅ ጓጉተን ነበር እናም በጨዋታ መልክ ወንዶቹን ጠየቅናቸው። በፌዝ በተሞላ መልክ የሰጡን መልስ ለሴቶች እምብዛም ፍላጎት እንደሌላቸው ያሳይ ነበር። ፍቅረኛዬ እንደቀልድ አንዱን 'ስታናድ' ስትለው ፈገግ ብሎ 'አዎ አናዳለሁ' ሲል መለሰላት።

በመቀላለድ አንድ ሁለት ብንባባልም መልሳቸው ጠቃሚ መረጃ አልሰጠንም። ምናልባትም ኩዊር ሴቶች የት እንደሚገኙ ማወቅ ያልቻልነው በራሳችን ችግር መሰለኝ። በዛን ጊዜ ናይሮቢን በደንብ አናውቃትም፤ ኩዊር ሴቶች የት እንደሚገኙ ለማወቅ ደግሞ ልትነግረን የምትችል ኩዊር ሴትም አልነበረችም። ይሁንና ኩዊር ሴቶች በብዛት የሚገኙበት ቦታ ባናገኝም በአልኬሚስት የነበረን ጊዜ አሪፍ ነበር። ባር እና ፓርቲ ለሁሉም ሰው የሚመች ቦታ ባይሆንም እንዲሁም በተለይም ለኩዊር ሰዎች ብቸኛ መገናኛ ይመስል እነዚህ ቦታዎች ብቻ መዘውተራቸው ችግር እንደሆኑ ባምንም ተሳታፊ በመሆኔ ግን ደስተኛ ነበርኩ።

ዳንስ የማይችሉ እግሮቼ ቢገድቡኝም ደነስን፥ አወራን፥ ተጫወትን.... ኖርን። ሳንፈራ፥ ስለደህንነታችን ሳንጨነቅ እና እንደጥንድ ሰው እንዴት ያየናል ብለን ሳናስብ ተዝናናን። በቃ ራሳችንን ሆነን ነበር።

በዛ ቦታ ኩዊር መሆን ያለመሳቀቅ ሲገለፅ እንዴት ደስ እንደሚል ተረዳሁ። በናይሮቢ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ሲላፉ፣ ሲደንሱ እና ሲጫወቱ ማየት ሰላማዊ ህይወት ምን ሊመስል እንደሚችል በትንሹም ቢሆን አሳየኝ።

በናይሮቢ

የተመሳሳይ ፆታ

አፍቃሪዎች ሲላፉ፣

ሲደንሱ እና

ሲጫወቱ ማየት


ሰላማዊ ህይወት

ምን ሊመስል

እንደሚችል

በትንሹም ቢሆን

አሳየኝ።



# ራስን በመቀበል የተገኘ የኩዊርነት ደስታ





ታሪኬ ለየት ያለ እንዳልሆነ አውቃለሁ፤ ብዙዎች እኔ ያለፍኩባቸውን ችግሮች እንዳለፉ እና እውነተኛ ማንነታቸውንና ተቀባይነትን ፍለጋ ብዙ ውጣ ውረድ እንዳሳለፉ ይገባኛል። ግን ይህ የኔ ታሪክ ነው፤

በልጅነቴ እውነተኛ ደስታ ተሰምቶኝ አያውቅም። ኮሌጅ ልገባ አካባቢ ሚስጥሬ ውስጤን እጅግ ያስጨንቀው ነበር፤ ይህም ጓደኛ ሊሆኑኝ ይችሉ ከነበሮች ሰዎች እንድራራቅ አድርጎኛል። ራሴን መቀበል ከባድ ነበር። በሀይማኖት እና ባህል እና በማንነቴ መሀል አጣብቂኝ ውስጥ ገባሁ። ራስን በመካድ፤ በፀሎት እና ኲዊርነቴን በመደበቅ የተሞላ ጦርነት ነበር።

ማህበረሰባዊ እና ሀይማኖታዊ ጫና እግጅ ገኖ በሚታይባት እና እንደኛ አይነት ሰዎች ታፍነው በሚኖርባት ኢትዮጵያ መኖሬ ውስጣዊ ጦርነቴን አባባሰው። ብችል የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነት ከላዩ ገፍፌ ባነሳው ደስታዬ ነበር፥ በወቅቱ ማንነቴ የሀይማኖት መሪዎች ስላሉ ብቻ መወገድ ያለበት ችግር እንደሆነ አምኜ ነበር። ግን ምንም ያህል ብሞክርም ማንነቴ መቀየር አልቻልኩም።


አመታት ከፈጀ የውስጥ ፍትጊያ እና ራስን ፍለጋ በኋላ ራሴን መቀበል ቻልኩ። የተፈጠርኩት በዚህ መንገድ ነው፤ ምንም ያህል ብክደው እና ልደብቀው ብሞክርም ይህን እውነታ መቀየር አልችልም። እውነተኛ ደስታን ማግኘት ከፈለኩ ራሴን መቀበል የመጀመሪያው እርምጃ ነበር።

ራሴን ወደመቀበል ያለው መንገድ ቀላል አልነበረም። በውስጤ የታተመ አመለካከትን መቀየርና የማህበረሰቡን ምልከታ አልፌ መሄድ ነበረብኝ። ግን በእያንዳንዱ እርምጃ የነፃነት እና የሀይል ስሜት እየተሰማኝ ነበር። ኲዊርነቴን እንደሸክም ሳይሆን ፍቅር እና ክብር የሚገባው የማንነቴ አንዱ አካል እንደሆነ ተቀበልኩ።


ራሴን በመቀበል ውስጥ ያገኘሁት ደስታ ህይወቴን የሚቀይር ነበር። ባህልና የማህበረሰቡ አመለካከት ቢይዘኝም በትክክለኛ ማንነቴ ውስጥ ነፃነትን አገኘሁ። በፍርሀት እና በሀፍረት ሳልታሰር በኩራት ኲዊርነቴን የምቀበል ደስተኛ ሰው ሆንኩ።

ዛሬ ላይ በሚቀበሉኝ እና በእውነተኛ ማንነቴ በሚያከብሩኝ ጓደኞቼ ተከብቤ እገኛለሁ። ትንሽም ቢሆን ደስ የሚል እና የሚረዳኝ ማህበረሰብ አግኝቻለሁ። በእያንዳንዱ ቀን ማንነቴን ለመቀበል ምን ያህል ፅናት እንደነበረኝ ራሴን አስታውሳለሁ በምስጋና እና ኩራት ይህን ስኬቴን አከብራለሁ።

ኲዊርነቴን በመቀበል ውስጥ የማህበረሰቡን እስር አልፎ የሚሰማ ነፃነት እና ሙሉእነት እንዲሰማኝ ሆኛለሁ። በዚህ ጉዞዬ ስቀጥል እንዲሁ እንዳለሁ በቂ መሆኔን ሁሌም በማሰብ ነው።




ራሴን
በመቀበል
ውስጥ
ያገኘሁት
ደስታ
ህይወቴን
የሚቀይር
ነበር።



# ጥበብ እና የኩዊርነት ደስታ





ጥበብ ለተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ከምትሰጠው ጠቀሜታ አንደኛውና ዋነኛው ብዬ የማምነው ደስታን ማስገኘት ነው። ይህን ያልኩበት ምክንያት ዕውቅና፣ ትምህርት፣ ሀብት፣ ብቻውን ሁሉንም ባዶነትን ስለማይሞላ ነው። “ጥበብ እንዴት የደስታችን ምክንያት ትሆናለች?” ከተባለ ሰዎች በተለይም በዚህ ኩዌር ማህበረሰብ ውስጥ ያለን ደስታችንን የምናጣበት ዋነኛ ምክንያት ራስን ሆኖ መኖር አለመቻልና በሌሎች መገለል ናቸው። እናም ጥበብ የተዳፈነ ስሜቶቻችንን የምናስተነፍስባት፣ በተለያዩ ማነቆዎች ምክንያት ልንኖረው ያልቻልነውን ሕይወት ወይንም እኛነታችንን እንዲሁም ልንተነፍሰው ያልቻልነውን እውነት ጥበብ ስትኖረው ስታወራው እያየን ተስፋ የምናደርግባትና ውስጣችን ሕይወት እየዘራች ደስ የምታሰኘን ልዩ ስጦታችን ናት ብዬ ስለማምን ነው።

እንደው ጥበብ በእኔ ዘንድ ያላትን ውለታ (ቦታ) ላለማሳነስ “በወፍ በረር” ለእኔ ያላትን ጠቀሜታ ላስቃኛችሁ። ጥበብ ለኩዌር ቤተሰብ ከመዝናኛነት ባለፈ ራሳቸውን የሚያዩባት፣ ተስፋ የሚሰንዱባት፣ የሚማሩባትና የሚያስተምሩባት መሳሪያ ናት! የሚያስተምሩባት ስል ለአዲሱ የኩዌር ትውልድ እኔ ማን ነኝ እና ምንድን ነኝ? ለሚለው ምላሽ መስጪያ ናት። ይህም ብቻ ሳይሆን በተለምዶ “ቀጥ” ለሚባሉት የህብረተሰቡ ክፍልም ስለ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ግንዛቤ ማስጨበጫ የምትሆን የሰዎችን አእምሮ በመያዝ (በመግዛት) በቀላሉና መረዳት በሚችሉበት መልኩ እውነታውን ማሳወቂያ መንገድም ናት።

በተለይም የዚህን ማህበረሰብ መኖር በራሱ ለማይቀበሉ፣ በሰይጣን ቁጥጥር ስር ሆነው ነው ለሚሉ፣ ዕውቀት ከማጣታቸው የተነሳ ነው ለሚሉ ጥበብ እያዋዛች እውነታውን ማለትም እንደማንኛውም ሰው በዚህች ምድር ላይ በየኃይማኖቱ አገልጋይ የሚል ሹመት ተሰጥቷቸው በፅድቅ እያገለገሉ ያሉ፣ የዓለምን ታሪክ ከለወጡ ባለ ምጡቅ አእምሮዎች መሃከልም እንዳሉ፣ ማፍቀርም መፈቀርም የሚችሉ የጤነኛ አእምሮ ባለቤቶችም እንደሆኑ፣ አስረግጣ ማሳያ መሳሪያ ናት።

ለምሳሌ ፊልምን ወይንም መፅሐፎችን ብንወስድ በሁሉም ዘንድ እንደሚታመነው ገፀ ባህሪያቱ የእውነተኛው (የገሃዱ) ዓለም ነፀብራቅ እንደመሆናቸው በዚያ ውስጥ ራሳቸውን እያዩ የሚበረቱበት የሚታነፁበት ብሎም የሚማሩበት ይኖራሉ። ሌሎች ደግሞ ዕውቀቱ ስለሌላቸው የሰዎች ማንነት ወይንም አፈጣጠር የሚያውቁበት አስተሳሰባቸውን የሚያሰፉበት ተጨማሪ ለማወቅ እንዲጥሩ ብርታት የሚያገኙበትን አጋጣሚ ታመቻቻለች። በዋናነት ወይም ጠቅለል ስናደርገው ጥበብ ለተገፉና ዕውቅና ለተነፈጉ እና ለታፈኑ ድምፆች ከፍ ብላ የምትሰማ ድምፅ በመሆን ታገለግላለች።

እስኪ እኔ ካየኋቸሁና ዘና ካልኩባቸው እናንተም ብታዩት ትዝናኑበታላችሁ ትማሩበታላችሁ ያልኩትን ጀባ ልበላችሁ። በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛ ፍቅር የሌለ እስኪመስል “ፍቅርን” በኮንትራት መለዋወጥ “ውሉ” ሲያልቅ ደግሞ እንደ ጠላት መተያየት እና ለበቀል መፈላለግ ግዴታ ነው የተባለ እስኪመስል መደበኛ የአኗኗር ዘይቤ ለሆነለት ለዚህ ማህበረሰብ አባላት ይጠቅማሉ ያልኩትን ላጋራችሁ። ተከታታይ ፊልሞች እና ቆየት ያሉ ቢሆኑም ሁለቱን Locked Up & Orange Is the New Black የሚባሉት ጥሩ ምርጫ ናቸው። ምነው ከእስር ቤት አልወጣ አልሽ እንዳትሉኝ ፍቅር የምትፈተነው በአሰልቺ ውይንም በማይመች እና በአስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ነው ብዬ ስለማምን ይመስለኛል ፊልሞቹ ምርጫዬ የሆኑት። ለፍቅር የሚከፈልን መስዋዕትነት ፍቅርን እንደ ሸቀጥ ለሚያዩና ዕቃቃ ጨዋታ ለሚመስላቸው የፍቅርን ኃያልነት እና ራስን መቀበል የሚያስከፍለው እና የሚያሳጣው ነገር

> **ጥበብ ለኩዊር ቤተሰብ ከመዝናኛነት ባለፈ ራሳቸውን የሚያዩባት፣ ተስፋ የሚሰንዱባት፣ የሚማሩባትና የሚያስተምሩባት መሳሪያ ናት!**

ቢኖርም የሚያስገኘውን የህሊና ዕረፍት ታዩበታላችሁ።


ሁሉም ሀገራት አናሳ የሆኑ ማህበረሰቦችን (minority group) የመጨቆኛ መሳሪያ ቢሆንም “የራሴ” የሚሉት ባህልና እሴት አሏቸው። ጥበብ ደግሞ የምትገለጠው በገሃዱ ዓለም ገፅታነት ነው ካልን እንደ እኔ አሁን ላይ የማይታሰብ ቢሆንም በራሴ ሀገር ሰዎች ደራሲነትና ተዋናይነትና ቢሆን ደስታዬን ይጨምረው ነበር። እንዲሁም ባህልና እሴቱ እንዳለ ሆኖ የተሰራበት ወይ ታሪኩ የተፃፈበት ድባብ የሀገሬን መልክዓ ምድር በሚያሳየኝ መልኩ ቢሆንልኝም ምርጫዬ ነው። የዚህም ምክንያት እኔ ልኖረው የምችለውን ሕይወት፣ ሊገጥሙኝ የሚችሉ ፈተናዎችን፣ ያሉትን ስጋቶች፣ ምቹ ሁኔታዎች፣ የምኖርበት ማህበረሰብ ስለ እኔ ያለውን አመለካከት የማይበት Bollywood ወይም Hollywood የተሰራ ፊልም ሳይሆን እዚሁ መገናኛ አዳማ ወይ ጎንደር ውስጥ በሀገሬ ልጆች የተሰራው ነው። ይህንን ስል አነፃፅሪ ከተባልኩ የተሻለውን መምረጤ እንጂ በሌሎች/ሌላ ሀገር የተከወነች ጥበብ ጥቅሟ በዜሮ የተባዛ ነው እያልኩ እንዳልሆነ ከላይ ያልኩትን ይያዝልኝ።



# ደስታን በስደት



የተሳሳተ ቦታ እንጂ የተሳሳትኩ ሰው አልነበርኩም። ኩዊርነት ሰላም ነው፤ ደስታ ነው፤ እሱንም አረጋግጫለሁ።



ከኢትዮጵያ ወደ ኬኒያ የመጣሁበት ቀን በኩዊርነቴ ታላቅ ደስታ ከሰጡኝ ቀናት ውስጥ አንዱ ነው። ኩዊር መሆን የደስታ ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ፍንትው አድርጎ ያሳየኝ ቀን ነው።

እዚህ ያለሁበትን ሁኔታ ከኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ ከነበረው ጋር ሳስተያየው የሰማይና የምድር ያህል ያለውን ልዩነት ያሳየኛል። ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ እራሴ ማውራት ማለትም ሌዝቢያን ነኝ ብሎ ለመናገር በጣም ከባድ እና አደገኛ ነበር። እድለኛ ሆኜ እዚህ ኬኒያ እንደፈለኩት በማንኛውም ቦታና ሰዓት ስለእራሴ ምንነት እና ስለ ኩዊርነቴ ማውራት እችላለሁ።

ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ የቁም እስረኛ እንደሆንኩ ነበር የሚሰማኝ ምክንያቱም እንደልቤ መውጣት መግባት ብችልም

በሀገሬ እንደፈለግኩኝ መንቀሳቀስ ብችልም ስለእራሴ ግን ማውራት አልችልም ነበር። እንዲያውም ጭራሽ መንቀሳቀስም የማልችልበት ደረጃም ደርሼ ነበር። ሁላችንንም ኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ያለን ሰዎች ሰቆቃ ውስጥ የከተተን ሐምሌና ነሐሴ አካባቢ የነበረው የሆሞፎቢክ እንቅስቃሴ እኔን ትልቅ አደጋ ውስጥ ነበር የከተተኝ። እንደአንድ በተለምዶ ወንዳወንድ የምትባል ሴት በነፃነት መንቀሳቀስ እንኳን እማልችልበት ደረጃ ላይ ደርሼ ነበር። መንገድ ላይም ራሱ ስንቀሳቀስ ፍራቻ እና ስጋት ነበረብኝ፤ ከአሁን አሁን መጡ፣ መቱኝ፣ ገደሉኝ የሚለው ፍራቻ ነበረብኝ። እዚህ መጥቼ ግን ማንም ማነሽ ብሎ የሚጠይቅ የለም፤ የፈለግሽውን መልበስና የፈለግሽውን ማድረግ ትችያለሽ። ይሄም ደስተኛ እንድሆን አድርጎኛል ምክንያቱም ያለ ስጋት ራስን ከመሆን በላይ ደስታ አለ ብዬ አላስብም።

እዚህ መጥቼ ደስታውንም ሰላሙንም ሳገኘው ሀዘኔም ጭንቀቴም ከማንነቴ ጋር የተያያዘ እንዳልነበረ ሳውቅ እረፍት ነው የሰጠኝ።

በተጨማሪም ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍቅረኛዬ ጋር እንደፈለኩኝ መሆን አልችልም። ካፌ ተቀምጬ ማውራት የማልችልበት ሰዓት ሁላ ነበር። እዚህ ግን ሰው ሁሉ የራሱ ጉዳይ ብቻ ላይ ነው የሚያተኩረው። ግፋ ቢል መንገድ ላይ ስትሄጂ ጥንዶች ናችሁ ብለው ይጠይቁናል። ከፍቅረኛዬ ጋር ወጣ ያለ ነገር ባናደርግም መንገድ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘን እና ተቃቅፈን እንሄዳለን፤ መንገድ ላይ ስንሄድም ሰዎች ደስ ትላላችሁ እና ምርጥ ጥንዶች ናችሁ ይሉናል እንጂ ምንም ዓይነት የገጠመን ነገር የለም። እንደውም በመልካም እንጂ በመጥፎ ዓይን የሚየየን ገጥሞን አያውቅም። ከጓደኛዬ ጋር ነው የምኖረው እና ቤት ያከራዩን ሰዎችም ይህን ያውቃሉ ግን ምንም ነገር አይሉም። እንደ እኛ ሀገር ስድብ የሚሰድብሽ ወይም የሚያስፈራራሽ የለም።

ሌላ ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ ይቅርና ከፍቅረኛዬ ከጓደኞቼ ጋር እንኳን ከፍርሃት የተነሳ በነፃነት ለመዝናናት አልችልም ነበር። ብዙውን ጊዜ የማሳለፍው ብቻዬን ቤት ውስጥ ነበር። አእምሮዬን በጣም ይጨንቀኝ ነበር፤ ፍርሃቶች ነበሩብኝ። ኩዊር በመሆኔ የሚደርስብኝ ተፅእኖዎች የጥላቻ ንግግሮች፣ ስድቦች፣ አስቁመው መንገድ ላይ ለምን እንዲህ ሆንሽ ለምን እንዲህ ለበስሽ ለምን እንዲህ አደረግሽ የሚሉት ነገሮች ነበሩ። እዚህ ማንኛውንም ልብስ ልበሽ፣ ማንነትሽን የሚገልፅም ቢሆን ልክ ቀስተደመና ያለበትን ልብስ እንኳን ለብሰሽ ብትንቀሳቀሺ ማነሽ ብሎ የሚጠይቅሽ የለም። ይህም የሚያሳየው ከእኛ ሀገር በጣም በተሻለ ሁኔታ የኩዊር ማህበረሰብ ተቀባይነት እንደአለው ነው። ለዚህም ይመስለኛል እኔ ኬኒያ ከመጣሁ ጊዜ ጀምሮ ወጣ ያለ ነገር ያላጋጠመኝ። ነገር እንደ ማንኛውም ሰው እና ዜጋ ኩዊር ሰዎችን ተቀብለውን እየኖርን ነው። ይሄም ደስ ይላል። ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰመረው ቀይ መስመር የለም ይህም እንደፈለኩት የመሆን ነፃነት ሰጥቶኛል።


እዚህ ከመምጣቴ በፊት የጭንቀቴ እና የአእምሮ ውጥረቴ ኩዊር በመሆኔ የመጡ ይመስለኝ ነበር። ምክንያቱም ኢትዮጵያ እያለሁ በጣም ጭንቀት ነበረብኝ። ራሴን መሆን አለመቻሌ ያመጣብኝ ነገር እንደሆነ ግልፅ አልሆነልኝም ነበር። ሰዎች ምን ይሉኛል የሚለው ነገር ብቻ በጣም ይረብሸኝ ነበር።

እዚህ መጥቼ የተማርኩት ነገር ግን ኩዊር መሆን ደስታ እንዳለው ነው። ለካስ ኩዊር መሆኔ አልነበረም ጭንቀት ውስጥ ከቶኝ የነበረው ይልቅስ ቦታው ነበር ደስተኛ እንዳልሆን ያደረገኝ። ደስተኛ ያልነበርኩት ኩዊር ስለሆንኩኝ ሳይሆን የነበርኩበት ቦታ ትክክለኛ ቦታ ሳላልነበረ ነው። እዚህ መጥቼ ደስታውንም ሰላሙንም ሳገኘው ሀዘኔም ጭንቀቴም ከማንነቴ ጋር የተያያዘ እንዳልነበረ ሳውቅ እረፍት ነው የሰጠኝ።

እኔ ይህንን ሁሉ ማለት የቻልኩት እዚህ ኬኒያ በመምጣቴ ነው። የተሳሳተ ቦታ እንጂ የተሳሳትኩ ሰው አልነበርኩም። ኩዊርነት ሰላም ነው፤ ደስታ ነው፤ እሱንም አረጋግጫለሁ።

# የራስ ፍቅር እና ደስታ ረዥም ጉዞ





ሌዚቢያን ነኝ ብዬ
መቀበሌን ለራሴ
ስነግረው ከዛ ሁሉ ጊዜ
በኋላ እንባዬን ማቆም
አቅቶኝ ስቅስቅ ብዬ
አለቀስኩ። እረፍት
ተሰማኝ! ራሴን ሆንኩ!

## ራሴን መቀበል እንዳለብኝ በማመኔ ከራሴ ጋር እርቅ አውርጃለሁ።

በዚህ የህይወት መንገድ ራስን መቀበል በጣም ከባድ ነው። ልጅ ሆኜ ማለት 10 ወይም 11 ዓመት ላይ ዝም ብሎ ተመሳሳይ ፆታን ማፍቀር ሳይሆን ማድነቅ መመቸት ይመስለኝ ነበር፣ ከዛ ከፍ እያልኩ ስመጣ እንደዛ ብቻ እንዳልሆነ እየገባኝ መጣ፤ 8ተኛ ክፍል ስደርስ እርግጠኛ ሆንኩ።

አንድ የክፍላችን ተማሪ ተመቸችኝ። ብዙ ወንዶች ያንዣብቡባታል፤ ለእኔ ግን የቅርብ ጓደኛዬ ናት። ክፍል ውስጥ አብረን ነን፤ ቤትም ስንሄድ መንገዱ እንዲረዝም እያወራን በረዥሙ መንገድ እንሄዳለን፥ ከዛ ደሞ ቆመን ብዙ እናወራለን፤ አያልቅም። መለያየት አንፈልግም። የተሰማን ስሜትማ ነበር ነገር ግን ማናችንም ደፍረን አላወራንም፤ ምንም አልፈጠርንም።

እስከ 10ኛ ክፍል እንደዚህ ቀጠለ የሚተነፍስም የሚሞክርም አልነበረም። ሁሉም ሰው "እናንተ አትለያዩም በቃ ምንድነው እንደዚህ" ይሉናል። አንዳንዴ ቁጣም አለው። መንገደኛው ሁሉ ያውቀን ነበር። እሷን የተመኘ ጎረምሳም በንዴት ያፈጥብኝ ነበር። የምፈልገው የኔ እንድትሆን ነው ግን መናገርም መጠየቅም አልቻልኩም፤ ምክንያቱ ደሞ በመጀመሪያ እኔ ራሴ ትክክል ነው ብዬ አልተቀበልኩም። ከዛ ይልቅ ትግሌ የነበረው ከዛ ስሜት ለመውጣት ለመርሳት ለመተው "በፍፁም እኔ እንደዚህ አይነት ሰው አይደለሁም" ብዬ መሸምጠጥ ነበር። በሰዓቱ ያላስተዋልኩት ደግሞ ወንድ ልጅን በዛ አይን ለማየት አለመቻሌን ነው።

ሲጀመር ማንም ሰው ተመሳሳይ ፆታ ስለማፍቀር ኖርማልነት አያወራም፤ ሁሉም የሚያወራውም የሚታየውም ስለተቃራኒ ፆታ አፍቃሪ ነው። ሲቀጥልም አልፎ አልፎ የምንሰማው የወንዶቹም የተወገዘ ነው፥ ሲወራም ተዋደው የሆኑት ሳይሆን ተገደው የገቡበት እርግማን እንደሆነ ነው የምንሰማው፣ ከዛ ውጪ ሌላ መረጃም የለም። ታዲያ ከየት አምጥቼ ምን ብዬ እራሴን እቀበላለሁ?

ወደዩኒቨርስቲ ስገባም ይሄው ነኝ... ጊዜው ሲያልፍ ሚጠፋ እየመሰለኝ ስጠብቅ ቆይቼ በመጨረሻ ይሄን ነገር ዘግቼ ትኩረቴን ትምህርት ላይ አደረኩ። የተመቹኝ ሴቶች ቢኖሩም አድናቂ ብቻ ሆንኩ። በዚህ መልክ የስራውን አለም ተቀላቀልኩ። ከተወሰነ ጊዜ በኃላ የሆነ ሁሉንም ነገር የሚቀይር ጉዳይ ተከሰተ...ባልታሰበ መንገድ ካንዷት ልጅ ጋር ፍቅር ጀመርኩ። የተምታታ ነገር! በጣም ከመዋደዳችን የተነሳ ሌላውን ረሳን። የሚያስታውቅ ፍቅር፤ በቃ የማይደበቅ! እንግዳም አይደለን ለዚህ ፍቅር? ከማህበረሰቡ እይታ ማምለጥ አልቻልንበትም። እናም የሚገራርሙ ምቶች አናታችን ላይ አረፉ። ለመቋቋም ሞከረናል ግን ሁለታችንም አልቻልነውም። ተለያየን ወደ ሌላ ሄደች ስም የሌለው ግንኙነታችን የሚሞቅ ነገር ነበረው ስትሄድ ብርዱ አንዘፈዘፈኝ መናገርም ለማንም ማስረዳትም አልቻልኩም። በሰዓቱ እኔም ታመምኩ ከዛ ለመውጣት ስል ግን ያገኘሁትን አጋጣሚ ተጠቀምኩ።

ማህበረሰባችን ራስሽን እንድትሆኚ አይፈቅድልሽም፣ ከዛ ደሞ አግቡ ውለዱ ይላል ያሳድግልሽ ይመስል! ቤተሰብም "ለምን አታገቢም?" ይልሻል። የማገባትን አይደለም "እኔ ተመሳሳይ አፍቃሪ ነኝ" ብል ራሱ ይቀበለኛል? በፍፁም! በጨዋታ በነገሮች መሃል ስለዚህ ጉዳይ ከተነሳ ጥላቻቸው የሚገርም ነው።

ቤተሰቦቼ እና ጓደኞቼ እንዲህ እንደሚወዱኝ እንደሚጨነቁልኝ ይህንን ጉዳይ ያወቁ እለት ብዬ ሳስብ ፍራቻው ልቤን ያርዳታል በእነሱ ሚዛን የሚገርም ቦታ አለኝ። "እስከመቼ?" ብዬ እጠይቃለሁ። ማንነቴን ስለማውቀው በጣም እንደሚጎዱ አውቃለሁ፣ ጥላቻቸውን

አይቼዋለሁ በዚህ ደሞ እኔም እጎዳለሁ ምክንያቱም በህይወቴ ሁሌም ቅድሚያ የምሰጣቸው ሰዎች ናቸው። መጎዳታቸውን አልፈልግም እነሱም ይህንን እንደማይፈልጉ አውቃለሁ፣ እንዲህ የሚሆኑልኝ የቅርብ ሰዎች እነሱን ላለማስከፋት እራሴን ባለመሆን እንዴት ዋጋ እየከፈልኩ እንደሆነ አለመረዳታቸው ያሳዝነኛል፤ እነሱ የፈለጉትን በሚሆኑበት ዓለም ለእኔ ራሴን መሆን አለመፈቀዱ እና ቦታ አለመሰጠቱ ያማል። አንዳንዴ ማንነቴን እንደሚጠረጥሩ አስባለሁ። ለምትወዱት ሰው ጥፋት ሲያጠፋ አስተባብላችሁ ወይም አያደርግም ብላችሁ እንደምትከላከሉለት ሁሉ እነሱም የሆንኩትን ቢያውቁም "እሷ እንዲህ አይደለችም አታድርገውም" እያሉ ማንነቴንን ይክዱልኛል።

እንዲህ አይነት መውደድ እየገደሉ ማዳን ነው ወይስ ምን እንበለው?

ራሴን ለቤተሰቦቼ መግለፅ የማይታሰብ ነው አደጋው ብዙ ነው። ስለዚህ በነፃነት ስለራሴ የምነግረው ሰው የለም ግማሹ ወሬ ለማሞቅ ሌላው መጠቀሚያ ለማድረግ የቀረውም ለመቀለድ ሲል ወሬውን በሚስጥር የሚይዘው አይመስለኝም። በርግጥ ጥቂት መልካሞች አይጠፉም፥ በራሱ ጊዜ ማወቅ ያለበት ሁሉ በውድም በግድም ያውቀዋል እስከዛው ግን እኔ ካወኩት በቂ ነው። ልናገር ብልም ለወሬ ካልሆነ ራሴን አወኩት እንጂ ራሷን ያወቀች የተቀበለች ፍቅረኛ የለችኝም። ማንን አፈቀርኩ ብዬ ነው ርዕሱንስ ማነሳው?

ከዚህ ጋር ተያይዞ በአለባበስ ነፃነቴ ማንንም አልሰማም። ከተመቸኝ እኔን ካልረበሸኝ በቂ ነው ለሌላው ደስታ የሚጨንቀኝን መልበስ አልፈልግም። በፊት ስራ ቦታ እንደ ሴት ልበሺ ጭቅጭቅ ነበር። በስራ ስትበረቺ ሁሉም ይረሳልሻል። በአለባበሴ እና በፀጉር ስታይሌ በርካታ አይነት አስተያየቶች ይደርሱኛል። የኛ ሰው እንዴትም ብትሆኚ አስተያየት መስጠቱ የማይቀር እንደሆነ ስለምረዳ የሚመቸኝን ስታይል በመልበስ ነፃነቴን አውጃለሁ። እናም ሳይወዱ ተቀብለውኛል ቢሆንም ቢሆንም ተመሳሳይ አፍቃሪነትን ግን ማወጅ ህይወት ላይ እንደመቆመር ሆኖ ነው የሚሰማኝ።

እኔ ወደማህበራዊ ሚዲያ የመጣሁበት ጊዜ ቀውጢው ጊዜ ነበር። ሁሉም ሰው መተማመን በፈራበት በነውጥ ውስጥ ቢያልፍም መተባበርና አይዞኝ መባባልን አይቼበታለው። እኔን የሚመስሉ በርካቶች እንዳሉ አወኩ ተዋወኩ ብቻዬን አይደለሁም፥ ለካ አንድ አይነት ክንፍ ያላቸው ወፎች አንድ ላይ ይበራሉ። ራስን የሚመስሉ ሰዎች ማወቅ እንዴት ደስ ይላል?

በዚህ ሁሉ ውስጥ ማንነቴን ልቀይረው እንደማልችል ዘግይቶም ቢሆን ገባኝ። ተፈጥሮን ራስን እንደመሆን ደስ የሚል ነገር የለም። ብዙ ተብሰልስዬ አዝኜ ፈጣሪዬን ሞግቼ ለምን ብዬ ራሴን ልረታው አልቻልኩም፤ እናም ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሌዚቢያን ነኝ ብዬ መቀበሌን ለራሴ ስነግረው ከዛ ሁሉ ጊዜ በኃላ እንባዬን ማቆም አቅቶኝ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ። እረፍት ተሰማኝ! ራሴን ሆንኩ! ዛሬ "ማነኝ? እንዴት? ለምን?" አልልም። ወደውስጥ ራሴን አይቼ እኔን እኔ ነኝ ብዬ በመቀበሌ ውስጤ ሰላም ነው። ራሴን መቀበል እንዳለብኝ በማመኔ ከራሴ ጋር እርቅ አውርጃለሁ።

በራሴ እፎይታ አግኝቻለሁ፤ እኔን በመሆኔ እኔን መሰሎች እንዳሉም መረዳቴ በብቸኝነት ከመጨነቅ እየታደገኝ ነው። በዚህ አጋጣሚ ታሪካችሁን ያካፈላችሁኝ፣ የራሴን ታሪክ በእናንተ ውስጥ እንዳይ ያደረጋችሁ፣ ያለፍኩበት ከልብ የነካችሁ፣ እጄን ባንድም በሌላም የያዛችሁ የኲዊር ቤተሰቦች አስተዋፅኦቻችሁ ብዙ ነው።


ወደውስጥ ራሴን አይቼ እኔን እኔ ነኝ ብዬ በመቀበሌ ውስጤ ሰላም ነው።





# የኔ ፍቅር፡ የኔ ኲዊር ደስታ

መብራቱን
አጥፍታ ደብዘዝ
ብሎ ክፍሉን
ያደመቀ ሻማ
አብርታ ከዛም
ለስለስ ያለ
የጊታር ዜማ
ያለው ሙዚቃ
ከፈተች።

ሁሉም የጀመረው ከረዥም እና አድካሚ ቀን በኋላ ዘና እንድትል ባደረኩላት የአንገት ማሳጅ ነው።

ፓንት ብቻ አድርጋ መሬት ላይ ባለ ተለቅ ያለ ነጭ ትራስ ላይ ቢጫ የሶፋ ትራስ ደርባ በእግሬ መሀል ተቀምጣለች። አንገቷን በቀስታ ማሸት ስጀምር በደስታ ታቃስታለች። እንደምትወደው የማውቀውን የአንገቷን ክፍል ማሸት ስቀጥል እሷም ማቃሰቷን ቀጥላለች።


በኋላ ግን ምንም የፀጉር ቅባት እንደሌለን ስላወቅን ፀጉሯን ውሃ ማስነካትን መረጥን። አንድ ላይ ወደትንሽዋ መፀዳጃ ቤት ገባን ሻወር እንድንወስድ ሀሳብ አቀረብኩ ወዲያው ግን ገንዳ ውስጥ መዘፍዘፍ እንደሚሻል ተረዳሁ። መብራቱን አጥፍታ ደብዘዝ ብሎ ክፍሉን ያደመቀ ሻማ አብርታ ከዛም ለስለስ ያለ የጊታር ዜማ ያለ ሙዚቃ ከፈተች። ክፍሏ ትንሽ ብትሆንም ገንዳው ደግሞ ይበልጥ ያንሳል። ለሁለታችን ሰውነት ግን በቂ ነው። ደገፍ አልኳት የጥርስ ብሩሽ የምናስቀምጥበትን እቃ ውሀ አድርጋበት ደረቴ ላይ አፈሰሰች። ሙቅ ውሃ ደረቴ ላይ ከዛም ወደሚስጥራዊ የሰውነቴ ክፍሎች ሲወርድ በትኩረት ትመለከታለች። እጆቿ በጀርባዬ ላይ ይርመሰመሳሉ። በስሱ ደረቴን ነካች። ከኋላዋ እንድሆን ቦታ እንድንቀያየር ጠየኳት ቦታዬን አሳልፌ መስጠቴ ቀላል አልነበረም ግን ይህ ምሽት ስለሷ ብቻ ነው።


ደረቴ ላይ ስትተኛ እግሮቼን ላይዋ ላይ ጠመጠምኩ፥ ጠባቧ ገንዳ ለሁለታችንም ዘና የሚያደርግ ቦታ የላትም። በስስት ውብ ጡቶቿን እና ደረቷን ማሻሸት ጀመርኩ። በእርጋታና እንክብካቤ፣ በጡቶቿ ውበት እየተደሰትኩ ደረቷን አሻሻለሁ። እርስ በእርሳቸው እንዲቀራረቡ እና ውሃው በሆዷ ላይ እንዲንሸራሸር የሚያስችል ዋሻ ስፈጥር ሳቋዋ አየሩን ሞላው። የሞኝ ጨዋታ ነው ብላ እንደምታስብ አውቃለሁ ነገር ግን ትረዳኛለች። ጣቶቼን በሚያምር እና በተጠቀለለ ፀጉሯ ውስጥ በፍቅር እያንሸራተትኩ በቀስታ ራሷን ማሸት ጀመርኩ። ውሃው ቀስ በቀስ ሲቀዘቅዝ ገንዳውን እንደገና ሞላነው። ሙሉ ምሽቱ የኛ ነው።

በመጨረሻ ከመታጠቢያ ገንዳው ውስጥ ወጣን። ውሃው በመታጠቢያው ወለል ላይ መፍሰሱን ስታይ ካላፀዳሁት አለች። ከአድካሚ ቀኗ በኋላ ዘና ማለቷ መቋረጡ ደስ አላለኝም። ግን የቆሸሸው መታጠቢያ ቤት ካልፀዳ ሰላም እንደማታገኝ አውቃለሁ። የጥርስ ብሩሾቻችንን ወደነበሩበት ስትመልስ እኔ ቤቱን መወልወል ጀመርኩ።

ጥሩ መዓዛ ያላቸውን ሻማዎች እና ዘና የሚያደርገውን ሙዚቃችንን ይዘን ወደ መኝታ ቤታችን ገባን። ብዙም ሳይቆይ ትኩረቴን ወደ እሷ መለስኩ፤ በእግሮቼ መካከል መሬት ላይ ተቀመጠች። ምሽቱን ሙሉ እሷን የፈለኳት ቦታ አገኘኋት። አንገቷን፤ ራሷን እና ትከሻዋን ማሻሸት ጀመርኩ። ወደ አልጋው ሄድን አሁን.ጀርባዋን በፍቅር ማሸት እችላለሁ። ማቃሰት ጀመረች እኔ ገና መጀመሬ ነው።

ሰውነቷን አዙሬ በጀርባዋ ተኛች፣ ራሷን ጭኔ ላይ አድርጋ ጋደም ብላለች። ፊቷን በዝግታ ማሸት ጀመርኩ። አይኖቿ ተከድነዋል። ሰውነቷ ሲፍታታ ይሰማኛል። ዓይኖቿ ለረዥም ጊዜ ተዘግተው ቆዩ። ቆንጆ ፊቷን እየዳበስኳት በትኩረት እያየኋት ነው። ምን እንደሚያስደስታት መከታተል ጀመርኩ። የምፈልገው ደስታዋን ነው። ከዛም ደግሜ ደግሜ  እሱን ማድረግ ቀጠልኩኝ።





ሙዚቃው ዝም አለ። በቀስታ አይኖቿን ከፈተች እና ፊቷ ላይ በተረጋጋ ፈገግታ፣ “እንዲህ ዘና ብዬ የማውቅ አይመስለኝም” አለች”፤ ግንባሯን ከዚያም ከንፈሯን በእርጋታ ሳምኳት።

እስካሁን ያልነካሁዋትን ቦታ ጠቆም አድርጌ ትኩረቴን ለሷ ደስታ መስጠት ላይ አደረኩ፤ በእርጋታ እጆቼን ወደ እሱ አንቀሳቀስኩኝ። እዛ አካባቢ በዝግታ መጫወት ቀጠልኩ። በቀስታ ማሸት። መነካካት። ጫፉን መዳበስ። “እንዴት እንደሆነ አላውቅም እሱ ጋር ስትነኪኝ የመነሳሳት ብቻ ሳይሆን የውስጥ መረጋጋት ሁሉ ይሰማኛል” አለች። አስቤበት ነው፤ ሆን ብዬ። ይሄ ምሽት ውስጧን ስለማዳመጥ ነው። ስለመረጋጋት ነው። በከንፈሯቿ እጫወታለሁ። መጀመሪያ ላይ ያዝ ብቻ። ከዚያ ወደ ውስጥ አመራለሁ። ልክ ጠርዝ ላይ ቀስ ብዬ እጫወታለሁ። ለመግባት በሰውነቷ ፍቃድ እስክትሰጠኝ ድረስ ጠበኩኝ። ከዛም ቀስ በዬ አጠገቧ እተኛለሁ። ከንፈሯን ሳምኩ። ምላሳችንም ተራ ደረሰው። ጣቶቼ ወደ እሷ የበለጠ ገቡ። ጣቶቼን በቀስታ ወደውስጥዋ ሳስገባ ያሰማችው ድምፅ ደስተኛ መሆኗን አረጋገጠልኝ። በእርጋታ ጣቴን ወደ ውስጥ ማስገባት እና ማስወጣት ጀመርኩ። ቫይብሬተር ብላ ጠየቀችኝ። አሁን ወደኋላ መመለስ የለም፤ በእርካታ እስክትንቀጠቀጥ ድረስ ቫይብሬተሩን መጠቀም አላቆምኩም። ስትጨርስ ቫይብሬተሩን ለማጥፋት ታገለች፤ ማጥፊያውን ማግኘት አልቻለችም፤ በርግጥ ማጥፊያው ቦታ ቀይሮ አልነበረም፤ ግን የሚንቀጠቀጡ እጆቿ ሊረዷት አልቻሉም። ተስፋ ቆርጣ ትታው እኔ ላይ ስትተኛ ተቀብዬ አጠፋሁላት።

በመጨረሻም አቀፈችኝ። ፀጉሯን እያሻሸሁ አስተኛሁዋት።


እንደተኛች አያት ጀመር፤ የራሷ ልታደርገኝ ስለመረጠችኝ እንዴት እድለኛ ነኝ? ከአድካሚ ቀኗ በኋላ እሷን ደስተኛ ማድረግ በመቻሌ እንዴት እድለኛ ነኝ? የኔ ፍቅር፤ የኔ ኲዊር ደስታ!


## “እንዴት እንደሆነ አላውቅም እሱ ጋር ስትነኪኝ የመነሳሳት ብቻ ሳይሆን የውስጥ መረጋጋት ሁሉ ይሰማኛል”

# የኲዊር ደስታ ለእናንተ ምን ማለት ነው?

## እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...





ኲዊር ደስታ ለእኔ ከማህበረሰቤ ጋር ስሆን ያለኝ ነፃነት ነው። ራስን መሆን ህገወጥ በሆነበት ሀገር ውስጥ ከሚመስሉሽ ሰዎች ጋር አብሮ መሆን ቅንጦት ነው።

ምን ደስተኛ ያደርገኛል? አሁን ላይ ልጄ። ራሴን የመቀበል ጉዞዬ የምትጠብቂው አይደለም። በማንነቴ ብዙም አልተቸገርኩም ማለት እችላለሁ።




ከሌሎቹ የተለየሁ መሆኔን የተገነዘብኩበት ቅጽበት ደስታን ይሰጠኛል፣ እንደ ማህበረሰብ አኗኗራችን እንድመረምር ያደርገኛል እናም ከተለመደው አስተሳሰብ ውጭ እንዳስብ ያስገድደኛል ምክንያቱም በመጀመሪያም የተለመደው አስታሳሰብ አይቀበለኝም ምክንያቱም ጌይ ነኝ።